# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንዎችና ስነ-ፅሁፍ - አማርኛትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**በደብረ ማርቆስ ከተማ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት**

**በ**

**ቦጋለ ስብሃቱ**

**ነሃሴ 2013 ዓ.ም**

**ጂማ ዩኒቨርሲቲ**

በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት


በጅማ ዩንቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዩጵያ ቋንቋ (ዋች) ና ስነ-ጹሁፍ አማርኛ ትምህርትክፍል


**ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ**

**የተዘጋጀ ጥናት**


**በቦጋለ ስብሃቱ**

**የጥናቱ አማካሪ ጥበቡ ሽቴ(ዶ/ር)**


**ነሃሴ 2013**

**ጅማ**

ጅማ ዩንቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማንቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጹሁፍ አማርኛተምህርት ክፍል

ድህረምረቃ መርሃ ግብር

ይህ በመንግስትና በግል ትምህርት ቢቶች የሚማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በቦጋል ስብሃቱ የተዘጋጀው ጥናት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት እንዲቀርብ ተወስኗል

የፈታኞችማረጋገጫ

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1አማካሪ መምህር | …………….. | ……….. | ……….. |
| 2የውጭ ፈታኝ | ……………….. | …………. | ………… |
| 3የውስጥ ፈታኝ | ………………. | ………… | …………… |

## በአጥኚው የቀረበ ማረጋገጫ

ይህ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በጅማ ዩንቨርስቲ ማህበራዊ ሳይንስናሂዩማንቲስ ህጋዊ ባለቤቱ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ ጹሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መረሃግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተስራ  የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎችም የሆኑና የጅማ ዮኒቨርሲቲ የጥናቱ ትንት ያለው መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

# ምስጋና

በቅድሚያ  ሁሉም ነገር ያለሱ ፍቃድ አልሁነምና ለዚህ ላደረሰኝ ፈጣሪየ ከእናቱ ከቅድስት ማርያም ጋር ምስጋናን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል ይህን ጥናት ከውጥኑ ጀምሮ በዚህ መልኩ ተጠናቆ እስኪቀርብ የጥናቱን ርዕስ በማስተካከል ከመነሻው ትክክለኛ መስመር እንዲይዝ በማድረግ የጥናቱን ረቂቅ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለመሰልቸት በጥልቀት ደጋግሞው በማንበብ፣ በጥናቱ የተለያዩ እርከኖች ላይ እጅግ ጠቃሚና ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ከመጠቆም ባለፈ እያንዳንዱን ቃል፣ሐረግ፤ዓረፍተ ነገር በጥንቃቄ በማየት ሰዋሰዋዊ የሆኑ የሆህያት ግድፈቶችን በማቃናታና በመጠቀም እንዲሁም በተለያዩ የምርምር ስነ-ዘዴያዊ ጉዳዮች ላይ እርማት ምክር የማሻሻያና አማራጭ ሃሳቦችን በመጠቆም ከፍተኛ ሞያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ፤ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ተነሳሽነትን ለመፍጠር በሚያስችል ትህትና የተሞላበት አባታዊ የማማከር ብልሃታቸውን አወንታዊ ሞያዊ ምክራቸውን ለሰጡኝለአማካሪዬ ለዶ/ር ጥበቡ ሽቴ  ልባዊ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡ ለዚህም ሙያዊ ምክራቸውም ታላቅ አክብሮትና አድናቆት አለኝ፡፡

ሶስተኛ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ወደ ኮምፑተር በመስብስብ  የፅሑፍ ስራዎችን ለተባበሩኝ ለእጩ ዶ/ር ይበልጣል እድሜ ከጤና ጋር ይስጥልኝ እያልኩ ከልብ የመነጨ ጥልቅ መስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

አራተኛ በጥናታዊ ስራው የመረጃ መሰብስብ ሂደት ላይ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ የጎዛምን አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና የሆህያት አካዳሚ ር/መምራንና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በሙሉና ፈተናውን በማረምና በማማከር ለተባበሩኝ ለመ/ር አንማው ታደለ ለአቶ ሙላት ስንሻው ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም በዚህ የትምህርት ቆይታየ ልጄን በመንከባከብ የአባትነት ፍቅሬንና ክትትሌን ላንደልኩበት ህፃን ናትናኤል ቦጋለና እሱን በመንከባከብ ላሳደገችው ለውድ ባለቤቴ ብርቱካን እርቁ ብዙአየሁ ክብርና ምስጋና መድሐኒዓለም አብዝቶ እንዲሰጣችሁ ምኞቴ ነው፡፡

**ምዕራፍአንድ vi**

መግቢያ ........................................................................................ 1
1.1 የጥናቱዳራ ........................................................................................ 1
1.2 የጥናቱመነሻችግር ........................................................................................ 3
1.3 የጥናቱአላማ ........................................................................................ 6
1.4 የጥናቱጠቀሜታ ........................................................................................ 6
1.5 የጥናቱወሰን ........................................................................................ 7
1.6 የጥናቱውስንነት ........................................................................................ 7
1.7 የጥናቱቁልፍቃላት.................................. Error! Bookmark not defined.
ምዕራፍሁለት ........................................................................................ 8
ክለሳድርሳናት ........................................................................................ 8
2.1 የመፃፍክሂልችሎታምንነት ........................................................................................ 8
2.2 የመፃፍክሂልየማስተማሪያአቀራረቦች ........................................................................................ 9
2.2.1 ውጤትተኮርአቀራረብ ........................................................................................ 9
2.3 የመፃፍክሂልትምህርትንአስቸጋሪየሚያደርጉተለውጦዎች ........................................................................................ 13
2.4 የጥሩፅሁፈትመመዘኛመስፈርቶች ........................................................................................ 14
ምዕራፍሶስት ........................................................................................ 19
የጥናቱዘዴ ........................................................................................ 19
3.1 የጥናቱንድፍ ........................................................................................ 19
3.2 የጥናቱተሳታፊዎች ........................................................................................ 19
3.3 የጥናቱናሙናእናየናሙናአመራረጥዘዴዎች ........................................................................................ 19
3.4 የመረጃመሰብሰቢያመሳሪያዎች ........................................................................................ 20
3.5 የመረጃአሰባሰብሂደት ........................................................................................ 20
3.6 የመረጃአተናተንዘዴ ........................................................................................ 21
ምዕራፍአራት ........................................................................................ 22
የውጤትትንተናማብራሪያ ........................................................................................ 22
4.1.የውጤትትንተና ........................................................................................ 22
ምዕራፍአምስት ........................................................................................ 30
ማጠቃለያመደምደሚያናየመፍትሔሃሳቦች ........................................................................................ 30
5.1. ማጠቃለያ ........................................................................................ 30
5.2 መደምደሚያ ........................................................................................ 31
5.3 የመፍትሔሃሳቦች ........................................................................................ 31

ምእራፍስድስት....................................................Error! Bookmark not defined.
ዋቢመጻሕፍት ........................................................................................ 33
ምእራፍሰባት.......................................................Error! Bookmark not defined.
አባሪዎች................................................................................................ 35
የሰንጠረዥማዉጫ.......................................................................................ix

## የሰንጠረዥማዉጫ

ሰንጠረዥ 4.1 የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንፅፅር በነጠላ ናሙና t-ቴስት ........ 22

ሰንጠረዥ 4.2 የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንፅፅር በነጠላ ናሙና t-ቴስት ........ 23

ሰንጠረዥ 4.3 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ንፅፅር በድርብ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 24

ሰንጠረዥ 4.4 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በይዘት መስፈርት የመፃፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ንፅፅር በድርብ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 25

ሰንጠረዥ 4.5 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአደረጃጀት መስፈርት የመፃፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ንፅፅር በድርብ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 26

ሰንጠረዥ4.6 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቃላት አጠቃቀም መስፈርት የመፃፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ንፅፅር በድርብ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 26

ሰንጠረዥ 4.7 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀም መስፈርት የመፃፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ንፅፅር በድርብ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 27

ሰንጠረዥ 4. 8 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በየስርዓተ ፅፈት መስፈርት የመፃፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ንፅፅር በድርብ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 27

# አጠቃሎ


የዚህ ጥናት ዋና አላማ በመንግስትና በግል ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈትሾ ማነፃፀር ነው፡፡ ይህን አለማ ከግብ ለማድረስ አነፃፃሪ ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ከመንግሰት ት/ቤቶች የጎዛምን አጠ/ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከግል ት/ቤት ደግሞ ሆህያት አካዳሚ ተመርጠዋል፡፡ በመንግስት ት/ቤቶች ካሉት ስምንት የመማሪያ ክፍሎች ጠቅላላ የጣ ንሞና ዘዴ ወረቀት ጠቅልሎ እጣ በማውጣት ተመርጠዋል፡፡ የግል ት/ቤቶች ካሉት ሁለት የመማሪያ ክፍሎች 40 ተማሪዎች በአጠቃላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና ከጥናቱ ተሳታፊዎች መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ በአግባቡ ከተደራጀ በኋላ ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስትና በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት የመረጃ መተንተኛ ሰልት ተተንትኗል፡፡ በትናትናው መሰረትም በነጠላ ናሙና ቴስት የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና በአማካኝ ውጤቱ ያለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ($t(39)=3.1981$ ⁞ $p<0.003$) ሲሆን ከመቶ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ አማካኝ ውጤት በሚጠበቀው መካከል ጉልህ ልዩንት መኖሩን ያመለክታል፡፡ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና በአማካኝ ያለው የጉልህነት ልዩንት ደረጃ ($t(39)= 2.655$, $p=0.0011$) ሲሆን ከመቁረጫ ነጠብ ($p>0.05$)በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይህም በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ አማካኝ ውጤትና በሚጠበቀው አማካኝ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩንት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ በመንግስት ት/ቤትና በግል ት/ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና ውጤት አማካኝ መካከል ያለውን ልዩንት ጉልህ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ መረጃው በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ውጤቱ ($t(78)= 4.085$ $p<0.0001$ ከመቁረጫ ነጥቡ$P=0.01$) አንሶ ተገኝቷል፡፡ በጉልህነት የጥንቃቄ ደረጃ ተሰልቶ ($^{a}=1\%$) ሆኖ ስለተገኘ መካከለኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም በመነሳት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ የተሸለ ደረጃ ላይ እንዳለ ተረጋግጧል፡፡ የህን መደምደሚያ መሰረት በማድረግም የልዩነት ምክንያትምን እንደሆነ በቀጣይ ጥናት ቢካሄድበት የሚል ጥቆማ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍአንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ በተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ተማሪዎች በአካባቢያቸዉ ያሉትን ነገሮች ለማወቅና ለመገንዘብ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማለትም የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የመጻፍና የማንበብ እንዲሁም የስነ-ልሳን እና የስነ-ጽሁፍ እዉቀታቸዉን ይጠቀማሉ (Nik, Rafidee, 2010፡60)፡፡ በመሆኑም የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሲዘጋጁ እነዚህን ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱ መሆን አለባቸዉ፡፡

የመፃፍ ክሂል ከሰው ልጆች የዕድገት ሂደት ጋር አብሮ በመጓዝ ጥንትም የነበረ፣አሁንም ያለ ፣ወደፊትም የሚኖር ነው፡፡እድገቱንም ስንመለከት በጥንት ጊዜ ሰዎች የተለያዩ የመጻፊያ ስልቶችን በመጠቀም በሸክላ ፣በቅጠል እና በድንጋይ ላይ ሃሳባቸውን በመግለጽ ለተግባቦትና ባህላቸውን ለትውልድ ለማስተላለፍ ከሚጠቀሙበት ስልት አንስቶ በአሁኑ ወቅት ዓለም እየተጠቀመበት እስካለው የኮምፒዩተር እና የኢንተርኔት ቴክኖሎጅ ድረስ በከፍተኛ ደረጃ እያደገና እየተወሳሰበ የመጣ እነደሆነ በmeillet(2017) ጥናት ላይ ተብራርቶ ቀርቧል ፡፡ ይህን የmeilletን ሃሳብ khieder(2012)በጥናታቸው ሲጠናክሩ የመጻፍ ክሂል የሰው ልጆች እድገት እንደሆነ ትኩረት ስጥተው ይናገራሉ፡፡ይህም ማለት የሰው ልጆች አዝጋሚ በሆነው የእድገት ሂድታቸው ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ተጠቅመው ያላቸውን ታሪክና ባህል አደራጅተው ባያስቀምጡና ለትውድም ባያስተላልፉ ኖሮ ማንነታቸው ሊታወቅ ባልቻለ ነበር፡፡

አማረ(2009ዓ.ም) Bourelle,(2009) እና Murphy(1996) ጠቅሰው እንደገለጹት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ስርዓት ተቀርጾለት በትምህርትነት መዋል የጀመረው ከዛሬ 2000 ዓመት በፊት ቢሆንም ክሂሉ የራሱ ናቸው የሚባሉ ዓላማዎችን ፣ማስተማሪያ ዘዴዎችንና መመዘኛ ስልቶችን ይዞ ብቅ ማለት የጀመረው ግን በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ነው፡፡ክሂሉ በተለይም ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በዓለም ላይ እየተጠናከረ የመጣ መሆኑን khieder(2012) አጽንኦት ሰጥተው ሲያብራሩ በ1950ዎቹ በትምርት ቤቶች ይሰጡ የነበሩት የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች በአብዛኛው የተማሪዎችን አዳምጦ የመናገርና የንግግር ክሂልን ትኩረት ያደረጉ ስለነበረ ለመጻፍ ክሂል የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ እንደነበር፤ነገር ግን የተግባቦ ታዊ የማስተማር ስነ ዘዴ በዓለም ላይ ተጽዕኖ ዕየፈጠረ ከመጣበት ከ1970ዎቹ ጀምሮ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂልን የማስተማር ዘዴ ጠቀሜታ እየታወቀና ተግባራዊ እየሆነ እንደመጣ ገልጸዋል፡፡□

የጽህፈት ክሂል ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ዉስጥ አንዱ ሲሆን በብዙ ምሁራን የጥናት ግኝቶች እንደተገለጸዉ ለተማሪዎች ከሌሎች ክሄሎች ይልቅ ከባድና ዉስብስብ እንደሆነ ነዉ፡፡ ለአብነት ያህል Al-Ahdal,Alfallaj, Al-Awaied and Al-Hattami (2014: 144;Baruha, 1985)ን ጠቅሰዉ የጽህፈት ክሂል ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች በተለየ መልኩ ዉስብስብ እንደሆነ ገልጸዉ ይህም የጽህፈት ክሂል በዉስጡ የሚያካትተዉ የፊደላት ቅደም ተከተሎችን በሚፈለገዉ መንገድ መጻፍ፣ ቃላትን የሰዋሰዉ ህጎችን በጠበቀ መንገድ መጻፍ፣ ትክክለኛ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገር ማዋቀር፣ ተገቢ ቦታ ላይ ተገቢዉን ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም፣ አያያዥ ቃላትንና ቅደም ተከታላዊ ምልክቶችን ለምሳሌ ተዉላጠ ስሞችን፣ መስተዋድዶችን፣ ወዘተ መተግበር፣ ሃሳቦችን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማደራጀት መግለጽ እና የመሳሰሉትን ንዑሳን ክሂሎችን ስለሚጠይቅ ለተማሪዎች እነዚህን በትክክል ለመተግበር አስቸጋሪ እንዲሚሆንባቸዉ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል እነ Nik,Hamzah, et al(2010: 55) ለተማሪዎች በጽህፈት ክሂል ወቅት እንቅፋት ከሚሆኑባቸዉ ነገሮች ዉስጥ ቋንቋዉን ከስነ ልሳን፣ ከሰዋሰዉ፣ ከዓረፍተ ነገር መዋቅር፣ ከመዝገበ ቃላት፣ ከፈሊጣዊ አነጋገሮች እና ከምሳሌያዊ አባባሎች አንጻር ቋንቋዉን በትክክል አዉቀዉ ከመተግበር ጋር የተያያዘ እንደሆነ በአገኙት ጥናታዊ ዉጤት አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህም ጋር አያይዘዉ ለተማሪዎች ከሌሎች ክሂሎች ይልቅ የጽህፈት ክሂልን ለማዳበር ይከብዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ ከንግግር ክሂል ይልቅ የጽህፈት ክሂል አንባቢዎች የተጻፈዉን ነገር ምንነትና መልዕክቱ ምን እንደሆነ እንዲጠይቁ ስለሚጋብዝና በምልክት ስለማይደገፍ የሚጻፈዉ ጽሁፍ በትክክለኛ ፊደላት፣ ስርዓተ ነጥቦችና የሰዋሰዉ አወቃቀር መደገፍ እንዳለበት ያብራራሉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ (Langan, 1987;Parker, 1993; እና Guning, 1998, በ Nik,Hamzah, et al,2010: 54) ተጠቅሰዉ የጽህፈት ክሂል ከንግግር ክሂል ይልቅ በጣም ዉስብስብ እንደሆነና ለተማሪዎች አስቸጋሪ እንደሆነ ትኩረት ሰጥተዉ ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ተማሪዎች በሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ያላቸዉ ችሎታ እየዳበረ በሄደ ቁጥር ለሚኖራቸዉ ዉጤታማነት የተግባቦት ክሂል በጣም ወሳኝ ነዉ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ሃሳቦችን በተባና ምርምራዊ በሆነ መልኩ ለመግለጽና ለሌሎች ለማስተላለፍ የሚያስችላቸዉን የጽህፈት ክሂል ከታች ክፍል ጀምሮ ማዳበር አሌ የማይባል ድረሻ አለዉ (Al-Ahdal,et at., 2014:)፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂልን ለማዳበር በጣም እንደሚቸገሩ ከላይ በተዘረዘሩት ጥናቶች መሰረት አድርጎ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ብቁና ዉጤታማ ጸኃፊ

ለመሆን ብዙ ጥረትና የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎችን እንዲሁም የመጻፍ ዝንባሌ እንዲኖራቸዉ ይጠይቃቸዋል፡፡ በመሆኑም የጽህፈት ክሂል ማለት ተማሪዎች እስክሪብቶን ወረቀት ላይ ማሳረፍ ወይም ቃላትን ወረቀት ላይ መደርደር ሳይሆን የተለያዩ ሃሳቦችን እንዴት ዉጤታማ በሆነ መልኩ ማቅረብ ወይም መግለጽ እንዳለባቸዉ ማወቅን የሚጠይቅ ክሂል ነዉ፡፡ስለሆነም የዚህ ጥናት ዉጤትም ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል ችሎታ ዙሪያ ያላቸዉን ጥንካሬና ክፍተት በማመላከት አስፈላጊ መረጃ እና ድጋፍ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

እንደ Pontes, Diniz and Martins-Reis (2013፡20) አገላለጽ ምንም እንኳን አራቱ የቋንቋ ክሂሎች የተቀናጁና ለተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ እዉቀትና በትምህርታቸዉ ለሚኖራቸዉ ስኬታማነት ወሳኝ ቢሆኑም የቋንቋዉን እዉቀት በጣም በተደራጀና ሰዋሰዋዊ መዋቅሩን በጠበቀ መልኩ ለሌሎች ከማስተላለፍ አንጻር ግን የጽህፈት ክሂል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

እንደ Nik, Sani, Chik, Jusoff and Hasbollah (2010: 8) አገላለጽ ዉጤታማና ጥሩ የጽህፈት ክሂል ተማሪዎች የሚከተሉትን ዋና ዋና አላማዎች እንዲያሳኩ ያደርጋቸዋል፡-

(1) ተማሪዎች የሰዋሰዉ መዋቅሮችን፣ የፈሊጣዊ አነጋገሮችንና መዝገበ ቃላዊ እዉቀታቸዉን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡
(2) ተማሪዎች የበለጠ ስለ ቋንቋዉ ደፋር እንዲሆኑና ከተማሩት ወጣ ብለዉ ነገሮችን በስፋትና በጥልቀት እንዲመረምሩ ያስችላቸዋል፡፡
(3) ሃሳቦችንና መልዕክቶችን በትክክልና ፍሰቱን በጠበቀ መልኩ ለሌሎች የሚያስተላልፉበትን የጽህፈት ንዑስ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡

በሌላ በኩል Javed, Juan and Nazli (2013) ጥናታቸዉ እንደገለጹት የጽህፈት ክሂል በተማሪዎች እዉቀትና ዉጤታማነት ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ፋይዳ እንዳለዉ አጽዕኖት ሰጥተዉ የሚከተሉትን ምክንያቶች ያቀርባሉ፡-

- የጽህፈት ክሂል የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል እንደሚያዳብር
- የተማሪዎችን መዝገበ ቃላት ብዛት የማወቅ አድማስ እንደሚያሰፋ
- የጽህፈት ክሂል ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ማለትም የማንበብ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎች እንደሚያዳብር ገልጸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እንድን ነገር ዉጤታማ በሆነ መልኩ የመጻፍ ችሎታ ለተማሪዎች ዉጤታማነት አመላካች እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ለምሰሌ Gesser and Studli (2001፣ በእነ Javed, et al., 2013) እንደተጠቀሰዉ ዉጤታማ የጽህፈት ክሂል አእምሮን

መፈተን ብቃት አለው። ምክንያቱም የተማሪዎች የቋንቋ ብቃት፣ የማስታወስ አቅምና የማሰብ ችሎታን ለመመዘን ይረዳል።

በሳል ጽህፈት የተደራጀ እቅድን በቂ የሆነ የሰዋሰዉ ችሎታና ሃሳብንና መልዕክትን ምክንያታዊና ተጠየቃዊ በሆነ መልኩ ማቅረብን ይጠይቃል። ይህም በመሆኑ የጽህፈት ክሂል ፊደላትን በትክክል መጻፍ፣ ቃላትን መመስረት፣ ስርዓተ ነጥቦን በተገቢዉ ቦታ መጠቀም፣ ሰዋሰዋዊ ስርዓትን መጠበቅና የሃሳብ ፍሰትን ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ አዋቅሮ መጠቀም የሚቀርብበት ዉስብስብ ክሂል ነዉ። ይህን አስመልክቶ Nik, Sani, et al (2010፡ 15) ላይ በጥናታቸዉ እንዳገኙት የጽህፈት ክሂል ለተማሪዎች አስቸጋሪ ስራ እንደሆነና በተለይም ሰዋሰዉና የቋንቋ መዋቅራትን በአግባቡ አለማወቅ ክሂሉን የበለጠ ዉስብስብና ከባድ እንዲሆንባቸዉ አድርጓል።

በተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ዙሪያ በዉጭ ሃገር በርካታ ጥናቶች ተካሄደዋል። ለምሳሌ Nik, Sani, et al(2010) በተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናት፣ በሳዉዲ አረቢያ የጁኒየር ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የጽህፈትና የንግግር ክሂላቸዉን በተመለከተ በእነ Al-Ahdal,et al (2014) የተደረገ ጥናት እና የተማሪዎችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂልን ከቃላት ምስረታ፣ ከዓረፍ ነገር አወቃቀር፣ ከሰዋሰዋዊ ስርዓት አጠቃቀም፣ ተረድቶ ከመጻፍና ከእጅ ጽሁፍ አንጻር የተደረገ ጥናት (Javed, et al., 2013)

በሌላ በኩል በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታን ለማጥናት Javed et al (2013) በአምስት ይዘቶች ማለትም የቃላት አጠቃቀም ፣የሰዋሰው አወቃቀር፣የዓረፍተ ነገር አመሰራረት ፣ሃሳብን ተረድቶ የመጻፍ ችሎታና የስርዓተ ጽህፈት ችሎታ ላይ በማተኮር ንጽጽራዊ ጥናት አድርገው ባገኙት ውጤት መሰረት በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች በሚማሩት ተማሪዎች መካከል የጎላ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ልዩነት እንደሌለ አስረድተዋል።

ወደ ሃገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ ምንም እንኳን ከአጥኝው ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸዉ ባይሆኑም አጥኝው ባደረገዉ የጥናታዊ ጽሁፍ ፍተሻ በጽህፈት ክሂል ዙሪያ የተሰሩ ጥቂት ጥናቶች እንዳሉ ለማስተዋል ችሏል። ከነዚህም ዉስጥ ካሚላ (2009) የመጻፍ ክሂል፣ የማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች የመጻፊያ ብልሃት ተዛምዶ፣ በይዘታዊ የጽህፈት ማስተማሪያ

ዘዴ ማስተማር ለክሂሉ መዳበር ያለዉ ሚና በሚል ርዕስ በሂሩት (2009) የተካሄደ ጥናት እና የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ አቀራረቦች ግንዛቤና አተገባበር ፍተሻ (ዘመን፣ 2009)፡፡

በተጨማሪም አጥኝው በመረጠው ርዕስ ላይ በአለማየሁ (1998) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በስነ-ልሳን ችሎታ፣በቋንቋ አጠቃቀም፣በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና በአንቀጽ አደረጃጀት ላይ ያላቸውን ልዩነት ለማወቅ የተደረገ ጥናት አግኝቷል፡፡የዚህ ጥናት ውጤትም እንደሚያስረዳው፣ አንጻራዊ በሆነ መልኩ በግል ትምህርት ቤት የሚማሩት ተማሪዎች የተሸለ የመጻፍ ክሂል ችሎታ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

ሃይማኖት(2005ዓ.ም) የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቀውን ያህል በጽሁፍ የመግለጽ ብቃት እንዳላቸው ለማወቅ በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት የመንግስት ትምህርተ ቤቶች ባካሄዱት ጥናት የተገነው ውጤት ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ብቃት ፣የእጅ ጽሁፋቸው አለመነበብ፣የቃላት ምርጫና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር እንዳለባቸውና የተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል ችሎታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አመልክቷል፡፡

ሰለሞን(2006 ዓ.ም) በቦንጋ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የግልና የመንግስትና ትምህርት ቤቶች የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች አንቀጽን አደራጅቶ ከመጻፍ ፣ከአንቀጽ ተገቢነት ፣ከህዳግ አጠባበቅና ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም አንጻር ያላቸውን ልዩነት ለማወቅ በተካሄደ ንጽጽራዊ ጥናት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ደረጀ(2007 ዓ.ም) የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሁፍ የመግለጽ ብቃት እንዳላቸው ለማወቅ በሶስት በአዲስአበባ በሚገኙ የግል ፣የመንግስትና የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ባካሄዱት ጥናት ውጤት ተማሪዎቹ በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል የፊደል ቅርጽን ጠብቆ በተነባቢ የእጅ ጽሁፍ ማቅረብና አንድ ሃሳብ ያለው የተሟላ አንቀጽ መጻፍ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸውና የጽሃፊት ክሂል ብቃት እንደሌላቸው አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም አጥኝው ከዚህ በፊት የተደረገ ጥናት ያገኘ ቢሆንም ጥናቱ የተሰራበትን የጊዜ እርዝማኔ፣ ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ የተለየ መሆኑ፣ ለጥናቱ የተመረጡት የተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ልዩነት እና የመማሪያ መጽሃፍቱም መቀየራቸዉን ከግምት ዉስጥ በማስገባት በመጨረሻም አጥኝው በጥናቱ ርዕስ ዙሪያ እንዲያጠና ያነሳሳው ምክንያት በብዙ ዓመታት

የማስተማር ልምዱእንዳስተዋለዉ ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል ዙሪያ ክፍተቶች እንዳሉባቸዉ አስተዉሏል፡፡

ስለሆነም ከላይ የተዘረዘሩትን ክፍተቶችና የአጥኝውን ግላዊ ምልከታን ከግምት ዉስጥ በማስገባት በደብረ ማርቆስ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ለማካሄድ ተነሳስታል፡፡ ይህ ጥናትም የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርጓል፡-

1.በመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የፅህፈት ክሂላቸው ምን ይመስላል?

2. በግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የፅህፈት ክሂል ችሎታ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

3.በመንግስት ትምህርት ቤትና በግል ትምህርት ቤቶች ተማራዎች መካከል በመጻፍ ክሂል ችሎታ ለዩነት አለ ወይስ የለም?

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በደብረ ማርቆስ ከተማ በሚገኙ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በማተኮር በጽህፈት ክሂል ችሎታ ዙሪያ የትኞቹ እንደሚሻሉ ማጥናትና ማነፃፃር ነዉ፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡-

- የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ምን እንደሚመስል ለመጠቆም
- የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የፅህፈት ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ ይገኛል የሚለውን መለየት
- በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶ ተማራዎች መካከል የመጻፍ ክሂል ችሎታ ልዩንት መኑሮን ማረጋገጥ

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ለባለ ድርሻ አካላት ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ እነሱም፡-

የጽህፈት ክሂላቸዉ ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች ይህን ክሂላቸዉን እንዴት ማሻሻል እንዳለባቸዉ ጥቆማ በመስጠት ለተማሪዎች እንደ ንግግር ሁሉ በጹሑፍም ተገቢውን ተግባቦት በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ ማከናውን እንደሚችል ተገንዝበው ክሂሎን ተግባራዊ እደሚያደርጎት መንሳሳትን ይፈጥርላቸዋል ፡፡መምህራን ባገኙት ፍንጭ ላይ በመመርኮዝ የማስተማር ዘዴዎቻቸዎን ለማየት እና ለማሻሻል እገዛ

ያደርጋሉ፡፡ስለዚህም በትምህርት ሒደት ያሎትን ችግሮች አጥንቶ የመማር ማስተማር ሒደቱ ሊሻሻል የሚችልበትን መንገድ ይጠቁማል ከመንግስትና ከግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በመጻሐፍት ክሂል ችሎታ የተሸላውን መርምሮ ለሊሎች ትምህርት ቤቶች ተሞክሮ ትምህርት ለመስጠት ይጠቁማሎ በቋንቋ ትምህርት በተለይ ለጽፍት ክሂል ማስተማሪያ አስፍላጊ የሆኑ መርጃ መሳሪዎችን ለማሟላት እዲችሎ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣሉ፡፡በተጨማሪም

ከርዕሱ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ወደ ፊት በሌሎች ተመራማሪዎች ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደብረ ማርቆስ ከተማ ዉስጥ በሚገኙ የጎዛምን መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የሆህያት አካዳሚ ከሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽር ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ አጥኝው ካለው የጊዜና የገንዘብ ዉስንነት የተነሳ ጥናቱ በከተማዉ ዉስጥ ያሉትን ሁሉምን ትምህርት ቤቶች እና ከጽህፈት ክሂል ዉጪ ያሉትን ክሂሎችን አያጠቃልልም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

በምርምር ስነ-ዘዴ ላይ ትክረታቸውን ያደረጉ አብዛኞቹ መፅሐፍት እንደሚገልፁት ይነስም ይብዛ ደረጃው ቢለያይም ማነኛውም ምርምራዊ ተግባር የራሱ የሆነ ውስንነቶች ወይም እጥረቶች ሊኖርበት እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡ በዚሁ ጥናትም አጥኝው ባደረጋቸው የክለሳ ድርሳናት ወይም 3 የተዛማጅ ፅሁፎች ፍተሻ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ምሁራን የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያላቸውን የመፃፍ ክሂል ችሎታ ደረጀውን በተመለከተ የተሰሩ ጥናትና ምርምሮችን በበቂ ሁኔታ ማግኘት አለመቻሉ ነው፡፡

# ምዕራፍሁለት

# ክለሳድርሳናት

## 2.1 የመፃፍ ክሂል ችሎታ ምንነት

የመፃፍ ክሂልን በተመለከተ በርካታ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይተረጉሙታል፡፡ ለምሳሌ እንደ (Meilet፡ 217) አገላልፅ መፃፍ ሃሳብን በሚነበብ መልኩ የማስተር፣ የመቃኘት፣ የማፍለቅና የመግለፅ ሂደት ማለት ነው፡፡ የ Meilet ሃሳብ እንደሚያመለክተው የመፃፍ ሃሳብን ለሌሎች የማስተላለፊያ አንዱ መንግድ ሲሆን የሚገልፀውን ሃሳብ ለማስፈፀም አገላልፆችን የመቃኘትና ተነባቢ በሆነ መንገድ የመግለፅ ሂደቶችን ያጠቃልላል፡፡

የመፃፍ ክሂል ማለት የአእምሮ ስራ ሲሆን ሃሳቦችን ለስረዎች ግልፅ በሆነና በሚገባቸው መልኩ በዐ. ነገርና በአንቀፅ አደራጅቶ የማቅረቢያ ስለት ነው፡፡ የመፃፍ ክሂል መረጃዎችን፣ ሃሳቦችን፣ እምነቶችን፣ ስሜቶችን፣ ክርክሮችን፣ ንድፈ ሃሳቦችን፣ የጥናታዊ ስራ ውጤቶችን ወዘተ. በቋሚነት ሰንዶ ለማስቀመጥ የሚረዳ ክሂል ነው፡፡ በዚህ ክሂል የሰው ልጆች ሃሳባቸውን፣ ስሜታቸውን እና ባህላቸውን ካለፈው አሁን ካለውና ከወደፊቱ ትውልድ ጋር የሚግባባበት የጥበብ ስራ ነው (Maurie,2016)፡፡

እንደ Nilket et al (2016) እና አለማየሁ (2007 ዓ.ም) አገላልፅ የመፃፍ ክሂል ሰዎች ለአካባቢያቸው ግንዛቤ የሚገኝበት ቀን በቀን ከማህበረሰቡ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ልምዶችን፣ ትርጉሞችንና እውቀቶችን የሚገኙበት ነው፡፡ የመፃፍ ክሂል አንዱ የተግባቦት ዓይነት ሲሆን ተማሪዎች ሃሳባቸውንና ስሜታቸውን በወረቀት ላይ የሚያሰፍሩበት እውቀታቸውንና እምነታቸውን አሳማኝ በሆነ መንገድ የሚያደራጁበትና መልክቶችንና ትርጉማቸውን በጣም በተደራጀ መልኩ በፅሁፍ የሚያስተላልፉበት ስልት ነው፡፡

Oluike (1979) በ (2012) እንደተገለፀው የመፃፍ ክሂልን ምንነት ከንግግር ክሂል ጋር በማነፃፀር ገልፀዋል፡፡ ይህውም የሰው ልጆች ሁሉ መናገርና መራመድን እንዲሁ በተለምዶ የሚለምዱት ሲሆን መፃፍንና ዋናን ለማወቅ ግን ከተፈጥሮአዊ ለመዳ የተለየ እንደሆነና ሰዎች ሆነ ብለው የሚማሩት ባህሪ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በዚህም ባህሪው አፍላቂ ክሂል ከሆነው ከንግግር ክሂል የተለየ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ከንግግር ሆነ ብሎ መማርን የማይጠይቅና ከአካባቢው ማህበረሰብ የሚለመድ ሲሆን መፃፍ ግን ሆን ተብሎ ትምህርት ቤት በመግባት የሚለመድ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የ Oluike(1979) ን ሃሳብ በመደገፍ ጌታቸው (2001)እንዲህ በማልትገልጹታል የመፃፍ ክሂል በባህሪው ክሂለ ብዙ ነው፡፡ የሐሳብ አደረጃጀት፤ የአንቀፅ አመሰራርት፤ የአረፍተ ነገር አወቃቅር፤ የቃላት አመሰራርትና አጠቃቅም በመፃፍ ክሂል ትምህረት ከሚፈልጉ ክሂሎች ምካክል በቀዳሚነት የሚጠቀስ ሲሆን ክሂሉእየፃፈ መማርን ይጠይቃል" በማለት ያስቀምጡታል፡፡

Nunan (2000) Kolade: (2012) እንደገለፀው የመፃፍ ክሂልን ምንነት ሲያስረዳ መፃፍ ሃሳብን በትምህርት ወይም በቋንቋ የመወከል ሂደት የሆነና የራሱ ሂደት ያለው እንደሆነ ነው፡፡ ሂደቱም አካልንና አእምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ ባህርያትን ለምሳሌ ይዘትን የአፃፃፍ ስልትን፤ የፅሁፍ መዋቅርን፣ የቃላት ምርጫን፣ የሃሳብ አንድነትን፣ ግጥምጥሞነትንና ተከታታይነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወንና ከማሰብ ጋር የሚቆራኝ ውስብስብ ሂደት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ይህን ክሂል የማቀፍ መረጃ የመፈለግ፤ የማርቀቅ የመከለስና የማስተካከል ሂደቶችን የሚከተልና በውስጡም የቃላት ፣የሰዋሰው፣የአጻጻፍ ስልት እውቀት የሚጠይቅ በመሆኑ ለመማር አስቸጋሪና ውስብስብ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ ማረው (1996) የመፃፍ ክሂል በሂደት የሚዳብር ሲሆን ሂዶቶችም ጠቅለል ባለ መንገድ ቅድመ መፃፍ እንደገና መፃፍ ማስተካከል እንደሆነ በፅሁፋቸው አስፍረዋል፡፡

በአጠቃይ ከላይ ከቀረበው የምሁራኑ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው መፃፍ በተከታታይ ልምምድ እንደገና እየጎለበተ የሚሄድ የራሱ ሂደት ያለው ሆን ተብሎ በመማር የሚገኝ ውስብስብ ክሂል መሆኑን ነው፡፡

## 2.2 የመፃፍ ክሂል የማስተማሪያ አቀራረቦች

የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር በሁሉም ቦታ በእኩል ደረጃ ውጤታማ የሚሆን የማስተማሪያ ዘዴ መፍጠርም አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ የተለያዩ ዘዴዎችና ቴክኒኮች በመጠቀም የመፃፍ ክሂልን መስተማር እንደሚቻል Adeyeni(2012) እና Hasson and Akhand (2010) ያስረዳሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በስፋት የሚታወቁትና በተግባር ላይ ያሉት እነዚህ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያገለግሉ የአቀራረብ ዘዴዎች ውጤት ተኮር አቀራረብ፣ ሂደት ተኮር አቀራረብ፣ ዘውግ ተኮር አቀራረብና ሂደተ ዘውግ አቀራረብ ተብለው በ4 ይከፈላሉ፡፡

### 2.2.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ

Adayeni (2012) እንደገለፁት ይህ አይነት አቀራረብ ትኩረቱ ተማሪዎች መጨረሻ ላይ በሚያቀርቡት ፅሁፍ ላይ ሲሆን ዘዴው በክፍል ውስጥ የሚከናወን ሆኖ አንድ በቅርፅ በስልቱና በቃላት አጠቃቀሙ የተመረጠ ፅሁፍ ለተማሪዎች በአብነት በማቅረብ ተማሪዎችም የቀረበላቸውን ፅሁፍ መሰረት በማድረግ ከስህተት የፀዳ ፅሁፍ እንዲፃፍ በማድረግ ነው፡፡ መምህሩም ትኩረት የሚሰጠው ለሰዋሰው ትክክለኛነት እንጂ ለተግባቦት አይደለም፡፡

እንደ Kolade (2012)፡ Adeyeni(2012) እና Hasson and Akhand (2010) አገላለፅ ውጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በመምህሩ ከተሰጣቸው አንድ ሞዴል ፅሁፍ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አንድ ያለቀለት ፅሁፍ እንዲያቀርቡ የሚያደረግ መሆኑን ይገልፃል፡፡ የዚህ አቀራረብ ዋና አላማም ለተማሪዎች ስለ ቋንቋው እውቀት ለመስጠት ነው፡፡ አተገባበሩም ተማሪዎች አንዳንድ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ለመቅዳት ከይዘቱ ጋር ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ያደርጋል፡፡ ከዛም ተማሪወች መምህሩ ያቀረበላቸውን ድርሰት በመቅዳት ከገለበጡ በኋላ ሞዴሉን ፅሁፍ በማስመሰል የተዋጣለት አዲስ ፅሑፍ በራሳቸው ወደ መፃፍ እንደሚያሽጋግራቸው የዚህ ንድፈ-ሐሳብ አቀንቃኞች ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ሂደት በኋላ ተማሪዎች የፃፉትን ፅኑፍ በመምህሩ የሚያቀርቡት የማስተካከያ ሃሳብ ወይም አስተያይት እንዲሰጣቸው ሳይሆን እንዲታረምና ውጤት እንዲሰጠው ነው፡፡ መምህሩም የተማሪዎችን ፅሑፍ ሲያርሙ ከይዘት ይልቅ ለቅርፅ በመስጠት ነው፡፡ ቅርፅ ላይ በማተኮር የሚሰጥ ግብረ መልስም በሆህያት፣ በስረዓተ ነጥብ፣ በቃላት ተገቢነት፣ በአረፍተ ነገር አመሰራረት በአንቀፅች አደረጃጅት በሰዋሰው ህግጋት ትክክለኝነት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማዳበር ውስንነት አለበት፡፡

### 2.2.2 **ሒደት ተኮር አቀራርብ**

ይህ አቀራርብ በዋናነት ዑደታዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ወደ ኋላ ወይም ወደ ፊት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላው ደረጃ በፅሑፍ ተግባራቸው እንዲስተካከሉ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ተግባራቸውን በሚተገብሩበት ጊዜ ፅሁፉን ፅፈው ከጨረሱ በኋላ እንኳ ወደ ቅድመ መፃፍ ተግባር ሊመልሱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዑደት ዋናው ነጥብ ፅሐፊውና የመፃፍ ሂደቱ ሲሆን የመምህሩ ሚና ደግሞ ተማሪዎችን በተለያዩ የመፃፍ ደረጃዎች መደገፍና ክትትል ማድረግ ነው፡፡

የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዋች በሒደት የመፃፍ ክህሎታቸውን ደረጃ በደረጃ እንድያዳብሩ የሚካሒድበት ነው፡፡ ይህ ዘዴ ለተማሪዋች ሰፊ ነፃነት የሚሰጥና ተማሪዋች

ለቅርፀ ሳይሆን ለይዘቱ ትኩረት እንዲሰጡ የሚያደርግ ዘዴ ነውKalad(2012) በሒደታዊ አቀራረብ ወቅት መምህራን ለተማሪዎች ፅሑፍ ማስተካከያ የሚሰጡት ረቂቅነት ላይ ይዞታን መሰረት አድረገው አንደሆን (Hasan and Akhand) 2010 ገልፀዋል፡፡

በሂደት ተኮር የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ አቅራረብ ላይ ከቀረቡትሒሳዊ አስተያየቶች ውስጥ ቀዳሚው ተቃዎሞ ሒደታዊ መፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ለፀሃፊው ማንነትና ለፁሑፍ ርዕስ ጉዳይ ትኩረት ሳይሰጥ ለሁሉም ተማሪዎች ለማንኛውም የፁሑፍ አይነት (አንድ ወጥ) ሒደትን የተከተለ ዘዴ ከመጠቀሙ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ለዚህም መሰረታዊ ምክንያቱ ለማህበራዊ አውድና ለፁሑፍ አላማ የሚሰጠው ትኩርት እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጀ እነዚህን ሂሳዊ አሰያየቶች ቢያስትናግድም በአሁኑ ጊዜ ሒደት ተኮር አቅራረብ ሰፊ ተቀባይነት በማግኘት በተግባር ላይ እየዋለ ይገኝል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ይህ አቅራረብ በፀህፈት ሒደት ላይ ተማሪዎች ሊከተሏቸው የሚገቡትን ቅደም ተከተላዊ ተግባራት ውይም ደረጃዋች በግልፅ ቀርበው ተማሪዎች በቀላሉ እዲረዷችው ሰለሚያሰችል በማለት ዳዊት (2008 ዓ.ም ) Badger እና White (2000) ን ጠቅሰው አብራርተዋል፡፡

ባጠቃላይ በሒደት ተኮር አቅራረብ ሀሳብ የመጀመሪያው ውስጥ ነገር ሲሆን አላማና አንባቢም ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ አቅራረብ ፈጠራን ይጠይቃል በትብብር መሰራት ላይ ያተኩራል፡፡ ከአንድ በላይ ፁሑፍች ይኖሩታል፡፡ በተጨማሪም ፁሑፍ እንዴት ተፃፈ? ” እናየፁሑፍን ይዘትና ሀሳብ እንዴት ማዳበር ይቻላል የሚሉ ጥያቄዋች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ Hasan and Akhand( 2010)

*2.2.3 ዘወግ ተኮር አቀራረብ*

ዘወግ ተኮር አቀራረብ ትምህርታዊ ፁሑፍች በሚዘወተሩባችው በክፍል ውስጥ ልምምደች ላይ ተማሪዋች በጋሃድ አለም ውስጥ የሚተገበሩትን ልዮ ልዮ የፁሑፍ አይነቶች ለምሳሌ፡- ልዮ ለዮ ዘገባውች /ሪፖርቶች/ የስራ ደብዳቤወች ርዕስ አነቅዶች የሂውት ታሪኮች ወዘተ… በክፍል ውስጥ እንዲለማመድ የሚበረታታ የአፃፃፍ ዘዴ ነው ዳዊት (2008) ይህ አቅራረብ ፀህፈት በማህበራዊ አውድ ውስጥ ይከናውናል የሚለውን ሀሳብ ያዳብራል ወይም የቀበላል፡፡ በተጨማሪም በሙሉ ንቃት ህሊና/Consciously/ በሚከናውን ማስመሰል /imitation/ እና ትንታኔ ነው የሚል ሲሆን ጆነር አቀራረብ ግልፅ (explicit) የሆነ የማሰተማር ሒደትን ያመቻቻል /Badger እና White( 2000) ተብሎም ይታመናል፡፡

አማረ (2009 ዓ.ም) Hyland (2009)እና Tangpermpoon (2008)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት ዘውግ ተኮር የመፃፍ ክሒል ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች የተለያየ ቅርፀ ያላችው ፁሀፍች

እንዲፀፍ እድል ይሰጣል፣ለአውድ ለአንባቢ ለልዮ ልዮ የፁሑፍ አይነቶች ለተግባቦታዊ አለማ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ስለሆንም ተማሪዎች ማህበረሰቦ በሚፈልገው መንገድ በመፃፍ ከማህበረሰቡ ጋር ውጤታማ የሆነ ተግባቦት እንዲፈጥሩ ያስችላል፡፡ በትረካ የመፃፍ ክሂል የማስተማር ስልት የመምህራን ሚናው መፃፍ ከቅርፀና ከይዘት አልፎ ከአንባቢ ጋር የሚያግባባ ቋንቋውም ግጥምጥንና ለመፃፍ አለማ ሰኬት የሚያበቃ እንዲሆን ማገዝ ነው ፡፡

ዳዊት(2008 ዓ.ም)Badger እና white (2000)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ይህ አቅራረብ እንደ ቀደሞች አቀራረቦች የተለያዮ ትችቶች ቀርበውበታል፡፡ ከእነዚህ የመቃወሚያ ሐሳቦች ውስጥ ቀዳሚው ፅሐፊው ስራን ለማከናውን አስፈላጊ ለሆኑት ሄደታዊ ተግባራት ዝቅተኛ ትኩረት መስጠቱ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዋችን እጅግ ለዝብተኛ አድርጎ መመልከቱ ሌላው ደካማ ጎኑ ነው ፡፡

**2.2.4 ሒደት ዘውግ አቅራረብ**

ይህ አቅራረብ ስያሜውን ያገኝው እንደ ዘውግ ተኮር አቅራረብ ፁሑፍ በማህበራዊ ሁኔታ ላይ የተገነባ ሲሆን በአንድ ፁሑፍ አማካኝነት አንድን የተውስነ አላማ ለማሳካት እንደ ፁሑፍ አይነት የሚያገለግሉ የቋንቋ አጠቃቀሞች ለይ የሚያተኮር መሆኑና ይህንንም ግብ ለማረስ የሚከተላቸው ሒድቶች ያሉት ስለሆነ ነው (Hasan and Akhand: 2010)

እንደ Hasan and Akhand (2010) ሂደት ዘውግ አቀራርብ ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮር ዘውግ ተኮር አቀራርቦች በተናጠል የየራሳቸው ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ያነን ክፍተት ለመሙላት የተፈጠረ የፅሁፍ ክሂል ማስተማሪያ አቀራርብ ነው፡፡ ለአብነትም  የሂደት ተኮር አቀራርብ አንዱ ደካማነት ለተማሪዎች ግብዓት አለማቅረብ ነው፡፡  ይህንን ክፍተት ለመሙላት መምህሩ የተለያየ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ግብአት እንዲያገኙ በቡድን ሆነው እየተወያዩ እንዲፅፉ ሊያደርግ ይቻላል ወይም ደግሞ ተማሪዎች ስለሚፅፉበት ርዕስ ጉዳይ ናሙና ፅሁፍ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ለተማሪዎች ግበዓት ማቅረብ ደግሞ የውጤት ተኮር አቀራርብ ጠንካራ ጎን ነው፡፡በዚህም የመፃፍ ክሂል የማስተማሪያ አቀራርቦችን በማዋኸድ መጠቀም የአንድ አቀራርብ ደካማ ጎን የሌለው አቀራርብ ጠንካራ ጎን ስለሚሆን በየራሳቸው ያለውን ክፍተት ለመመልከት ያስችላል በማለት ያስረዳል፡፡

Hasan and Akhand (2010፡81) ሂደተ ዘውግ አቀራርብ ከላይ ያቀረቡት የመፃፍ ክሂል የማስተማሪያ አቀራርቦችን አጣምሮ የያዘ በመሆኑ የትኩረት አቅጣጫው ሶስቱንም አቀራርቦች የሚዳስስ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ለሚፅፉት ፅሑፍ በግባትነት የሚያገለግል አንድ የተወሰነ መረጃ ማቅረብ ከውጤት ተኮርና ዘውግ ተኮር አቀራርብ ጋር የሚመሳሰል

ሲሆን ተማሪዎች እንዲይዙት የፈለጉትን የአፃፃፍ ስልት እንዲጠቀሙ ማድረግና መምህሩ በተደጋጋሚ በየደረጃው ድጋፍ ማድረግ ደግሞ ከሂደት ተኮር አቀራርብ ጋር ያመሳስለዋል፡፡በተጨማሪም ንደ ውጤት ተኮርና ዘውግ ተኮር አቀራርብ የቋንቋው አገልግሎት ላይ ማተኮሩ እንደ ዘውጋዊ አቀራርብ የፅሁፍ ተግባርና አላማ ላይ ማተኮሩ እንደ ሂደት ተኮር አቀራርብ በቋንቋው አገልግሎት ላይ ማተኮሩ ፅሁፉን በደረጃ በደረጃ ማዋቀር ላይ ማተኮሩ ተማሪዎች እንደችሎታቸውና አቅማቸውየሚፅፉበት መሆኑ ተጠቃሽ ነው፡፡ መምህራን ይህ የአቀራርብ ዘዴሌሎችን አቀራርቦች አጣምሮ የያዘ በመሆን እያንዳንዱን አቀራርብ በተናጠል ከመተግበር ይልቅ እንደ ላይ በማዋሀድ መጠቀም በተለይ ለጀማሪ ፅሐፊዎች የበለጠ ተጠቃሚ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

## 2.3 የመፃፍ ክሂል ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተለውጦዎች

ተማሪዎች የመፃፍ ክኂል በአግባቡ እንዳይማሩና እንዳያዳብሩ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ብዙ ተለውጦዎች እንዳሉ ብዙ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለአብነት ያህል Nik et al (2010) ባደረጉት ጥናት የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታ ወይ ኂላ ከሚጎትቱ ነገሮች ውስጥ ዋንኛው ተማሪዎች ቋንቋውን ከመጠቀም ጋር ካለሙያው ክፍተት ጋር ያልተያያዘ እንዳይሆን አፅዕበኖት ሰጥተው ተሻግሯል፡፡የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ክፍተት ማለት ተማሪዎ በተተወ ውስተጥ ሰዋሰውመ ግረፈተ-ነተሰዋሰውን አግባቡ አለማዎቀ ያላት አጠቃቀም ችግር ሃረጋት እና ግረፈት -ነገሮችን በትክክል አለመስረት የቋንቋ ሰዋሰው ህጎች አለመጠበቅ የፈሊጣው አነጋገሮችን ትርጉም ከማወቅ ጋር የተያያዘ ችግሮች እና ሌሎች እንዲሆነን ጥናት አድረጎ ምሁራ ገልፀዋል፡፡

ከዚህበተጨማሪ መምህራን ተማሪዎችን የመፃፍ ከሒል ለማስተማሪያ ከፍተኛ ፍተሻ እንዲገጥማችሁ Nik et al (2010) በጥናታችሁ ሪፖርት አድርገዋል፡፡ ይህም የሚሆንበት በአንዱ በኩል አንዳንድ መምህራን ይህን ክሂል ለማስተማር በቂ የሆነ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት የሚጎድሉት ሲሆን ሌሎች ደግሞ ክሂሉን በአግባቡ ለማስተማር በቂ እውቀት እና ስለሌላቸው ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ራሳቸው የመፃፍ ክሂሉን ተሎ ለመልመድ ና ለመተግበር ስለሚቸገሩ ነው፡፡በሌላ የጥናት ግኝት /2013/ እዳጋለጡት ለተማሪዎች የመፃፍ ክሂል መዳበርና ማደግ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ነገሮች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚገኙት ደካማ የመማር ማስተማር ሒደት ውጤት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የመጡበት የቤተሰብ መስራት ማለትም የቤተሰቦዎች የገቢ ምንጭ የቤተሰባቸው የትምህርት ደረጃ ፤የቤተሰባቸው መኖሪያ /አካባቢ ወዘተ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው በአፅዕኖት ተናግረዋል፡፡/2010/በ12ተኛ ክፍል

ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት  የጥናታቸው አካል የነበሩት ተማሪዎች በእንግሊዘኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሒል ደካማ አፈፃፀም እንዳላቸው አረጋግጠነዋል ። እንዳጥኝዎች አገላለፅ ተማሪዎች በመፃፍ ክሂል ላስመዘገቡት ደካማ አፈፃፀም ዋነኛው ምክንያት ተማሪዎች ከ7ተኛ ጀምሮ ስለ መፃፍ ክሂል ማደግናመሰልጠን የቋንቋውን አጠቃቀም በተመለከተ ወሳኝ ሚና ያላቸውን መሰረታዊ መመዘኛዎችን በበቂ ሁኔታ እየተለማመዱ እየተማሩ  አለመምጣታቸው ነው፡፡

በሌላ በኩል አለማየሁ(1998 ዓ.ም)Byren (1988)ን ጠቅሰው  እደገለፁት በመፃፍ ክሒል ትምህርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ  የሚያስፈሩ ተለውጦዎች በሶስት የሚከፈሉ ሲሆኑ እነሱም  ስነ- ልቦናዊ ችግረች (ከተማሪዎች ዝግጁነት፣ፍላጎት፣አመለካከት፣ቁርጠኝነት፣ ወዘተ ጋር የተያያዙ-ተፅዕኖዎች) ስነ-ልሳናዊ ችግሮች (ከቋንቋው አጠቃቀም ክፍሎች አመራረጥ ፣አረፍተ-ነገር አመሰራረት ወዘተ ጋር የተያያዘ ችግሮች እና ስነ-አእምሮታዊ ችግሮች ከተማሪዎች እውቀት ፣አረዳድ፣ልመድ፣ፈጠራው አስተሳሰብ ወዘተ-ጋር የተያያዘ-ተፅዕኖዎች) ናቸው፡፡

## 2.4 የጥሩ ፅህፈት መመዘኛ መስፈርቶች

የመፃፍ ክሒል በባህሪው ዘርፍ ብዙ ነው፡፡ይህም ሲባል በውስጠ የቃላት አመራረጥ ፣የዓረፍተ-ነገር አመሰራረት ፣የአንቀፅ አወቃቀር የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የመሳሰሉትን ለመፃፍ ክሂል የሚያስፈልጉ ነጥቦች አካቶ የሚይዝ የክሂል ዘርፍ ነው ለማለት ነው፡፡ ይህን ሀሳብ መነሻ በማድረግ አንድ ፁሁፍ ከሌላው የተሻለ ነው ወይም ጥሩ ፁሁፍ ነው ብሎ የመለየት ሞሁራንመስፈርቶችን መጠቀም ተገቢ እንዲሆን ይስማማሉ፡፡ለአብነት ያህል ዳዊት (2009 ዓ.ም እና 2010) Nik et al (2010) ጥሩ የመፃፍ ባህሪያት መስፈርቶች ካለው ከዝርዝራቸው ውስጥ ዋና ዋናዎችን እደሚከተለው በዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

### *2.4.1 በቂ ሐሳብ ወይም ይዘት*

በአንድ ጥሩ በሚባል ፁሑፍ ውስጥ በቂ ሀሳብ ማፍለቅ እያንዳንዱ አንቀፅ ሀያን ቃል መያዝና ይህን ሀይለ ቃል በበቂ መዘርዘር  ዓረፍተ ነገሮች በማብራራት ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪ ፁትፍ አላማውን ያገናዘበ ማስረጃዎች የተደገፈ ግልፅና ፣ማራኪ መሆን ይገበዋል፡፡ይህ እንዲሆንና ስለሚፃፈው ነገር በጥልቀትና በዝርዝር  ለማቅረብ የተፈለገውን አለማስተላለፍና ምንአይነት ቋንቋን መጠቀም እንደሚገባ ለመወሠን በቅድሚ ይዘቱን መረዳትና በቂ የሆነ ሀሳብ ሊኖር ይገባል፡፡

### *2.4.2 የቋንቋ አወቃቅር*

የቋንቋ አጠቃቀም በዋናነት ከተገቢ የስወስው አጠቃቀምና አገባብ አንፃር ቢታይ የሚቀል ነው፡፡ይህም ሲባል በፁሑፍ ሀሳብን ለአንባቢያን ለማስተላለፍ ትክክለኛውን የሰዋሰው ስርዓት መከተልን ያመለክታል፡፡ይህንንም ባየ /1887አ.ም/ የአንድ ቋንቋ ስርዓት ከድምፅ አሰካክ እስከ ሃረግ አመሰራረት ድረስ የሚያሳይ ሳይንስን ሰዋሰው እንለዋለን በማለት ይገለፃል፡፡በመሆኑም በመፃፍ ተግባር ላይ ተማሪዎች የሚጠቀሙት ቃል፣ሀረግና አረፍተነገሮች /በቁጥር፣በጾታ፣ በመደብና በጊዜ/ የተስተካከለና ከሰዋሰውስርአቶች የፀዳና አንባቢን የማያደናቅፍ መሆን አለበት፡፡

### 2.4.3 የቃላት አጠቃቀም

ለፁሑፍ ቋንቋ የምንጠቀመው መደበኛ የሆነ ቃላትን ና በንግግር ወቅት የምንጠቀማቸውን ቃላት የተለየ መሆን አለበት፡፡ይህ ማለት በንግግር ወቅት የምንጠቀማቸውን ቃላት በመፃፍ ጊዜ አንጠቃቅም ለማለት ሳይሆን በፁሁፍ ወሰን የቃላት አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው በድምፅ ቅላጤ፣በአካል እንቅስቃሴና በፊገጽታ ስለማይታገዝ ፀሀፊው ሃሳቡን በትክክል ለማስተላለፍ በሁሉም ህብረተሰብ የሚታወቁና መደበኛ የሆነ ቃላትን ቢጠቀም የተሻለ ነውለማለት ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪም ከኢ- መደበኛ የቃላት አጠቃቀም ከሃራም /ፀያፍ ቃላት ፣የአራዳ ቃላት፣ የተሰለቹ ቃላት፣የዘን ቃላትና ከቃላት ፅረጽ የፀዳና የመስለትን ችግሮች ማስወገድ የጥሩ ፀሑፍ ሌላኛው መግለጫ ባህሪው ነው(ዳዊት 2009 አ.ም/፡፡

### 2.4.4 ስርአተ - ፅህፈት

ስርአተ-ፅህፈት ሲባል በውስጡ ከፁሑፍ አጠቃላይ ወሚፀር ገፅታ ጀምሮ ከሆህያት መጠንና ቅርፅ ፣ከመስመር አጠባበቅ የቅኝን ግራ ህዳግ አጠባበቅ ና ስርአተ ነጥብን አጠቃቀም ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ሲሆን አጠቃላይ የቋንቋውን የአፃፃፍ ቅርፕ የሚያካትት ነው /ዳዊት 2008አ.ም/

### 2.4.5 የሀሳብ አደረጃጀት

አንድ ጥሩ ድርሰት መግቢያ ሃተታና መደምደሚያ አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ከአንጽ አንቀጽ የተዋቀሩ ዐረፍተ-ነገሮች ተያያዥነትና ተለጣጣቂነት ባለፈው ሁኔታ ዋናውን ንውሳን ሀሳብና ተጠያቂው በሆነ መንገድ ተደራጅተው ከሃሳብ ድግግሞሽ መጠራት በፀዳ መልኩ መቅረብ መቻል አለባቸው ፡፡እንደአለማየሁ (1999 አ.ም )አገላለፅ ሃሳብን ማደራጀት ሲባል አንድ ፀሃፊ ለመፃፍ ሲነሳ ምክንያት እንዳይልና ሁሉ በፁሑፍ ውስጥ ያሉ ሃሳቦችም ምክንያታቸውም

አደረጃጀቶች ሊኖራቸው ይገባል ።ይህ ማለት አንድ ፅሁፌ የሚያነሳቸው ሃሳቦች በአስማኝ ምክንያት ተደግፈው ተጠቃሚ አደረጃጀትን ተከትለው መቅረብ አልባቸው ለማለት ነው።

### 2.5 በመፃፍ ክሒል ችሎታ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ቀኝት

የዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ዓላማ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የዘጠኛ ክፍል ተማሪዎች በመፃፍ ክሂል ላይ ያላቸውን ችሎታ ማነፃፀር ነው። በመሆኑም አጥኚው ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች ለማየትና ለመዳሰስ ሞክሯል። በዳሰሳውም መሰረት Ponts et al (2013:833) በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች ምካከል በሚገኙ 61 የአራተኛና የአምስኛ ክፍል ተማሪዎች ምካከል ያለውን የእንግሊዘኛ ቋንቋ የማንበብና የመፃፍ ክሂልችሎታ ለማወቅ ባደረጉት ዳሰሳዊ ጥናት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግሰት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሸለ የማንበብም ሆነ የመፃፍ ክሂል አፈፃፀም እንዳላቸው አረጋግጠዋል። እንደ ጥናቶቹ አገላልፅ በግል ትምህርት ቤቶች ያሉት ተማሪዎች በክሂሎች ላይ የተሻለ አፈፃፀም ያሳየበት ምክንያት ተማሪዎች የመጡበት ቤተሰብ መሰረት በመንግሰት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ከመጡበት የቤተሰብ መሰረት በገቢ ምንጫቸው፣ በትምህርት ደረጃቸው በአኗኗር ሁኔታቸው የተሻለ እንደሆነ አስረድተዋል።

የእነ Ponts(2013) ጥናት በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል የሚማሩ ተማሪዎች ላይ የተሰራ መሆኑ ከአጥኚዎች የጥናት ርዕስ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ሁለቱ ጥናቶች በመካከላቸው ብዙ ልየነቶች አሏቸው። ስለሆነም የእነ Ponts ጥናት በአራተኛና በአምስኛ ክፍል ተማሪዎች የተደረገ መሆኑ የአጥኚዎች የጥናታቸው ትኩረት በሁለቱ የቋንቋ ክህሎቶች ማለትም በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች ላይ መሆኑንና ጥናታቸው የተካሄደው በውጭ ሁገር መሆኑ ነው።

በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን የእንግሊዘኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል ችሎታ ለማጥናት Javed et al (2013፡ 129) 44 ተማሪዎችን በናሙናነጥ በመምረጥ በዋናነት በአምስት ይዘቶች ማለትም የቃላት አጠቃቅም፣የሰዋሰው አወቃቅር፣ የዓረፍተ ነገር አመሰራርት፣ ሐሳብን ተረድቶ የመፃፍ ችሎታና የስረዓተ ፅህፈት ችሎታ ላይ በማተኮር ዳሰሳዊ ጥናት አድርገው ባገኙት ጥናት መሰረት በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች በሚማሩት ተማሪዎች መካከል የጎላ የመፃፍ ክሂል ችሎታ ልዩነት እንዳላቸው አስረድቷል።

ይህ ጥናት ከአጥኝው ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የተሰራ መሆኑና አጥኝዎች ተመሳሳይ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መጠቀማቸው ሲሆንየሁለቱ ጥናቶች ልዩነት ደግሞ ከጥናቱ አላማዎች አንፃር የእነ Javed et al{ ጥናት ትኩረት ያደረገው በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል በከተማና በገጠር ተማሪች ምካከል የመፃፍ ክሒል ችሎታ ልዩነት እንዳለ ማየት እንዲሁም የጥናታቸው የክፍል ደረጃ በአስረኛ ክፍል ላይ የተደረገ መሆኑ ነው፡፡

ሰለሞን (2006 ዓ.ም) በቦንጋ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የግልና የመንግስት ትምርት ቤት የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ የፅህፈት ክሂል የትኞቹ የተሻሉ እንደሆኑ ለማወቅ ከተማሪዎች እና ከመምህራን በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ከተማሪዎች በፈተና የተሰበሰቡትን መረጃዎች አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅመው ከተነተኑ በኂላ ባገኙት ውጤት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆኑ አስረድተዋል፡፡ በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመማሪያ መፀሐፍት፣ የመምህሩ መምሪያ መፀሐፍ ለሁለተኛ እርከን ደረጃ የተዘጋጁ የተለያዩ ሰነዶች በትምህርት ቤቱ ውስጥ በመረጃነት ያለመቀመጥና መምህራን ክፍል ውስጥ ከማስተማር በስተቀር ተማሪዎች በተለያዩ ዘዴዎች ለፅሕፈት ትምህርት ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩ ሚያደርጉት ጥረት አናሳ በመሆኑ ለተማሪዎች የመፃፍ ክሒል ችሎታ ዝቅተኛ ውጤት ተጠቃሽ ምክንያቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

የሰለሞን ጥናት ከአጥኝው ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያለው ቢሆንም የሚለያባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነሱም ጥናቱ የተካሔደበትን የክፍል ደረጃ፣ ቦታ፣ ጊዜ፣የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና የመተንተኛ ዘዴዎች ናቸው፡፡

አለማየሁ ተመስገን (1998 ዓ.ም) በአስራ አንደኛ ክፍል በሚማሩ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መካከል በፅህፈት ክሒል የትኞቹ የተሻለ ችሎታ እንዳለቸው ለመለየት ባካሔዱት ጥናት ከተማሪዎችና ከመምህራን የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን የተደረሰበት ውጤት አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የተሸለ የመፃፍ ክሒል ችሎታ እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡ለዚህም ዋናው ምክንያት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ለትምህርት በተለይም ለመፃፍ ክሒል ያላቸው ፍላጎት የሚሰጣቸው የክፍልም ሆነ የቤት ስራዎች የመስራት ዝንባሌአቸው መምህራን ለክሒሉ የሚሰጡት ትኩረት ከግል ትምህርት ቤቶች ጋር ሲነፃፀር አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ የአለማየሁ ጥናት ከአጥኝው ጥናታዊ ፅሑፍ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ተዛምዶ ያለው ሲሆን በጥናቱ ዳራ እንደተጠቀሰው የሚለይባቸው በርካታ ነጥቦች አሉ፡፡ ለምሳሌ ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ፣ ጥናቱ የተካሄደበት የክፍል ደረጃ፣ ጥናቱ የተካሄደበት አመተ ምህረት/ጊዜ፣

የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች እና የአለማየሁ ጥናት የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የስነ-ልሳን የቋንቋ አጠቃቀም ስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የአንቀፅ አደረጃጀት ችሎታቸውን የሚፈትሽ በመሆኑ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አለማየሁ የተጠቀሙት ለመምህራን እና ለተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሁም የመፃፍ ክሂል ፈተና ብቻ መሆኑና መረጃውም ከተማሪዎች ብቻ የሚሰበሰብ መሆኑና አለማየሁ የተጠቀሙት የመረጃ አተናተን ዘዴ ሁለቱንም ማለትም መጠናዊ እና አይነታዊ ሲሆን አጥኚው ግን የሚጠቀመው መጠናዊ መረጃ መተንተኛ ዘዴ መሆኑ፡፡

ደረጀ (2007) የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በፅሑፍ የመግለፅ ብቃት አላቸው በሚል ርዕስ በሶስት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የግል፣ የመንግስትና የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ባካሔዱት ጥናት ውጤት የተማሪዎቹ የመፃፍ ክሒል ችሎታ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑንና በደረጃውም የሚጠበቅባቸውን ያህል የፊደል ቅርፅ ጠብቆ በተነባቢ እጂ ፅሑፍ ማቅረብና አንድ ሃሳብ ያለው የተሟላ አንቀፅ መፃፍ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸውና የፅህፈት ክሒል ብቃት እንደሌላቸው አመልክተዋል፡፡

ሃይማኖት (2005 ዓ.ም) የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቀውን ያህል በፅሑፍ የመግለፅ ብቃት አላቸው በሚል ርዕስ በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ባካሔዱት ጥናት የተገኘው ውጤት ተማሪዎች ሃሳባቸውን በፅሑፍ የመግለፅ ብቃት የእጅ ፅሁፋቸው አለመነበበ የቃላት ምርጫና የስርአቱ ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች እንዳሉባቸውና የተማሪዎች የመፃፍ ክሒል ችሎታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አመልክቷል፡፡

የአጥኚው ጥናት ከሃይማኖት(2005ዓም)ጥናት9ኛ ክፍል ጋር የሚያመሳስለው በመፃፍ ክሒል ችሎታ ላይ ማተኮሩ ሲሆን ጥናቱ በተካሄደበት ቦታ፣ ጊዜና በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ ብቻ መካሔዱ ከአጥኚው ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ የደረጀ(2007) ጥናት ደግሞ በመፀሐፍ ክሒል ችሎታ ላይ ማተኮሩ ከአጥኛው ጥናት ጋር ቢያመሳስለው የተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ቦታና የትምህርት ቤት አይነት (የመንግስት፣ የግልና የህዝብ ትምህርት ቤቶች ስላካተተ) ከአጥኚው ጋር የተለየ ያደርገዋ፡፡

# ምዕራፍሶስት

# 3. የጥናቱዘዴ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ አጠናን ዘዴ የሚቀርብበት ነዉ፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ንድፍ፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደትና የጥናቱ አተናተን ስልቶች ምን ምን እንደሆኑ እና ለምን እንደተመረጡ ጥናቱ የሚወስደው ጊዜ እና ገንዘብ ግልጽ በሆነ መንገድ እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂል የትኞቹ የተሻለ ችሎታ እንዳላቸዉ መመርመርነዉ፡፡በመሆኑም ያለዉ (2009) እንደገለጹት ለዚህ ጥናት አመቺ ሆኖ የተገኘው የጥናት ንድፍ አነጻጻሪ ጥናት ነዉ፡፡ ምክንያቱም ይህ ንድፍ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቡድኖች መካከል በአንድ በተወሰነ ተለዋዋጭ ላይ ያላቸዉን መመሳሰልና መለያየት ለማጥናት ያስችላልና ነዉ፡፡ ማወዳደሩ ትረካና ገለጻን ተከትሎ ወይም መጠንን በሚያመለክቱ የተለያዩ ስታትስቲካዊ ዘዴዎች ሊሆን ችሏል፡፡ በዚህ ጥናትም መረጃው በፈተና ተሰብስቧል፡፡ ስለሆነም በፈተና የተቀናጀው መረጃ በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች

በዚህ ጥናት ዋነኛ ተሳታፊዎች በ2013.ም ተመዝግበዉ በግልና በመንግስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸዉን የሚከታተሉ የ9ኛ ክፍል ወንድና ሴት ተማሪዎች ናቸው፡፡

## 3.3 የጥናቱ ናሙና እና የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች

በመጀመሪያ ትምህርት ቤቶቹን ለመምረጥ በደብረ ማርቆስ ከተማ ዉስጥ አንድ ብቻ የ2ኛ ደረጃ የግል ትምህርት ቤት ያለ በመሆኑ ይህ ትምህርት ቤት በአላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴ የተለየ ሲሆን በከተማዉ ዉስጥ ካሉት ሶስት የ2ኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል ደግሞ በቀላል የእጣ ንሞና አመራረጥ ዘዴ አንድ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተወሰደ ነው፡፡ የክፍል ደረጃ አመራረጥን በተመለከተ ለጥናቱ በሚመረጡ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ካሉት ሁለት የክፍል ደረጃዎች ማለትም የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል መካከል ለጥናቱ የተወሰደው 9ኛ

ክፍል ነዉ። የክፍል ደረጃዉ የተለየበት ምክንያት አጥኝው በማስተማር ላይ ያለበት የክፍል ደረጃ በመሆኑና የችግሩን ግዝፈትና አሳሳቢነት በመረዳት የ9ኛ ክፍል በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተለይቷል።

በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ለመምረጥ ከተወሰዱ ሁለቱ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ላሉት ተማሪዎች አኩል እድል ለመስጠት በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 40 ተማሪዎች ተመርጠዋል።

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት ዉስጥ የጹሁፍ ፈተና ከጥናቱ ተሳታፊዎች አስፈላጊዉን መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል።የጥያቂውን ተገቤነት ከዚህ በፊት በጽፍት ክሂል ላይ ጥናታችውን የስሩ ሰዎችን በማየትና በመጠየቅ በተጨማሪም Jacobs et al{1981:30} ለይ ተወስዶ በዳዊት (2008) የተተረጉመዉና በአጥኝው ተግባራዊ የተደረገ የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ፈተና ማረሚያ መስፍርትን ተጠቅሚል።

### *3.4.1 የጽህፈት ክሂል ፈተና*

በዚህ ጥናት ቀዳሚ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለዉ የጽህፈት ክሂል ፈተና ነዉ። ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሚዘጋጀዉ በአጥኝው ሆኖ የተመረጠበትም ምክንያት የሁለቱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ፈተናዉን ከተፈተኑ በኋላ የሚያሳዩትን የጽህፈት ክሂል ችሎታ ለማነጻጸር ስለሚያስችል ነዉ። ፈተናዎቹም የጥናቱን አላማዎች መሰረት አድርገዉ የሚዘጋጁ ሲሆን የመጀመሪያዉ ፈተና የሚያተኩረዉ ተማሪዎቹ የአማርኛ ፊደላትን ወደ ጎን ከግዕዝ እስከ ሳብዕ እና ወደ ታች ከበ እስከ ፐትክክል መጻፋቸዉን ለማረጋገጥ የሚዘጋጅ ሲሆን ሁለተኛዉ ፈተና ደግሞ ተማሪዎቹ በሚፅፉአቸው የአንቀፅ ድርሰቶች ውስጥ የሚከተሉትን መሰረታዊ ነጥቦች በማካተት አንቀፆቻቸውን እንዲያቀናጁ የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ ስርዓት መጠበቅ፤ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀም መቻል፤ይዘቶችን መጠበቅ፤በተጨማሪም (የፆታ፣የመደብ፣የቁጥር፣የተሳቢ አመልካች) ጠብቀዉ አንቀጽ የመጻፍ ችሎታቸዉ ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽና ለይቶ ለማወቅ ነው።

## 3.5 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

በመጀመሪያ የፍቃድ ደብዳቤ ከሚሰራበት ትምህርት ቤትበመጠየቅ ለየትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን የጥናቱን አላማና የሚያስገኘዉን ጠቀሜታ በመግለጽ የሚፈልገውን ለጥናቱ ግብዓት ይሆኑኛል የሚላቸውን መረጃዎች ለማግኘትና ለመሰብሰብለጥናቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑ

ተማሪዎችን ለማግኘት ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ወደጥናት መስኩ ገብቷል፡፡ በመቀጠል ለመምህራንና ለተማሪዎች የጥናቱን አላማና ጠቀሜታዎቹን በተመሳሳይ መልኩ በማስረዳት እንዲሁም ፍቃደኝነታቸዉን በመጠየቅና በማረጋገጥ ወደ መረጃ መሰብሰቡ ገብቷል፡፡ በመጨረሻም አስፈላጊ የሆኑትን የጥናቱን መረጃዎች በጥናቱ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከጥናቱ ተሳታፊዎች ተሰብስቧል፡፡በኋላም መረጃዎቹ ለመጨረሻዉ ጥናት ዝግጁ እንዲሆኑ በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በመጀመሪያ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚሰበሰቡት መረጃዎች የጥናቱን አላማዎች መሰረት አድርጎ ለትንተና በሚያመች መልኩ እንዲደራጁ ተደርጋል፣ ከዚያም እንደ መረጃዎቹ ባህሪ መጠናዊና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ይተነተናሉ፡፡ ማለትም በፈተና የሚሰበሰቡት መረጃዎች በመጠናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (በቲ-ቴስት፣ በፐርሰንት) ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍአራት

## የመረጃ ትንተና ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል የትኞቹ የተሻለ ችሎታ እንዳላቸው መመርመር ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስም ከጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ለመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካኝነት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ይህ ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰቡ መረጀዎች የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ተተንትኖአል፡፡

### 4.1.የመረጃ ትንተና

የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ “የምንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ምን ይመስላል?” የሚል ነበር፡፡ ጥያቄውን ለመመለስ መረጃው በገላጭስታስቲክስና t-ቴስት ተተንትኗል ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.1 ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ4.1 የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንፅፅር በነጠላ ናሙና t-ቴስት

| ትምህርት ቤት | ናሙና | አማካኝ /m/ | መደበኛ ልያት /sd/ | የሚጠበቅ አማካኝ ውጤት/63.25/ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የ ”t” ዋጋ t-value | የነፃነት ደረጃ /df/ | ጉልህነት በባለ ሁለት ጫፍ/p/ |
| የመንግስት | 40 | 59.875 | 6.674 | -3.198*** | 39 | 0.003 |

***p<0.01

ከሰንጠረዥ 4.1 ገላጭ ስታትስቲክስ መረዳት እንደሚቻለው ከተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና የሚጠበቅ አማካይ ውጤት /µ=63.25/ ሲሆን የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት /m፡ 59.875/ ነው፡፡ ከዚህም ለመረዳት እንደሚቻለው የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካኝ ውጤት ከሚጠበቀው አማካኝ ውጤት በ (5.509) አንሶ ይታያል፡፡ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማካይ ውጤትም በአማካኝ ያለው ልዩነት ሲታይ መደበኛ ልይይት I sd=6.674

|ነው. ይህም የሚያመለክተው የእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት በአማካኝ ውጤቱ ከ I m=59.875 I በ|6.674| ያህል ወደ ታች ወይም ወደ ላይ እንደራቀ ነው፡፡

የመንግስት ትምሀርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ፈተና አማካኝ ውጤትና በሚጠበቀው አማካኝ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ መረጃው በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ውጤቱ (t=(39)=3.1981፣ P<0.003) ከመቁረጫ ነጥብ I p= 0.01 I አንሶ (ከሰንጠረዥ 4.1) ይገኛል፡፡ የመንግስት ትምሀርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ፈተና አማካኝ ውጤትና ከሚጠበቀው አማካኝ ውጤት ምካከል በሰታትሰቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡

የትንትናውን ውጤት መሰረት በማድረግ የመንግሰት ትመሀርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ምን ይመስላል?፤ የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ዝቅተኛ ነው የሚል መልስ አግኝተናል፡፡ ምክንያቱም የመንግስት ትምሀርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከሚጠበቀው አማካኝ ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ፡- የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ደረጃ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የሚል ነበረ ጥያቄውን ለመመለስ መረጀው በገላጭ ስታስቲክስና በነጠላ ናሙና ቲ- ቴስት ተተንተኗል፤ ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.2 ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ4.2የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንፅፅር በነጠላ ናሙና t-ቴስት

| **ትምሀርት ቤት** | **ናሙና** | **አማካኝ** /m/ | **መደበኛ ልያት** /sd/ | **የሚጠበቅ አማካኝ ውጤት/63.25/** | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የ "ቲ" ዋጋ t-value | የነፃንት ደረጃ /df/ | ጉልህነት በባለ ሁለት ጫፍ/p/ | |
| **የግል** | 40 | 66.625 | 8.040 | 2.655*** | 39 | 0.011 | |

**p<0.05

ከሰንጠረዥ 4.2 ገላጭ ስታትስቲክስ መረዳት እንደሚቻለው ከተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና የሚጠበቅ አማካይ ውጤት / μ=63.25 / ሲሆን የግል ትምሀርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት /m፡ 66.625 / ነው፡፡ ከዚህም ለመረዳት እንደሚቻለው የግል ትምሀርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካኝ ውጤት ከሚጠበቀው አማካኝ ውጤት በ (3.375 ) በልጦ ይገኛል፡፡ የግል ትምሀርት ቤት ተማሪዎች አማካይ ውጤትም በአማካኝ ያለው ልዩነት ሲታይ መደበኛ ልይይት Isd=8.040 I ነው፡፡

የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይቱ የሚያመለክተው የአንዳንድ ተማሪ ውጤት ከአማካኝ ውጤቱ ማለትም I m=66.625 Iበ 8.040 I ያህል እንደራቀ/ እንደወረደ ነው፡፡ በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካኝ ውጤትና በሚጠበቀው አማካኝ ውጤት ምካከል ያለው ልዩነት ጉልህ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ መረጃው በነጠላ ናሙና t-ቴስት ተሰልቶ ውጤቱ በ (t(39)=2.655, p=0.011 ከመቁረጫ ነጥብ P<0.05. መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት ምካከል በስታትስቲክስና ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

የትንትናውን ውጤት መሰረት በማድረግ የግል ትመህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?፤ የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል የሚል መልስ አግኝተናል፡፡ ምክንያቱም የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከሚጠበቀው አማካኝ ውጤት ጉልህ ልዩነት አላደረገምና፡፡

የሶስተኛው መሰረታዊ ጥያቄ ፡- በመንግስት ትምህርት ቤትና በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ምካከል ለመፃፍ ክሂል ችሎታ ልዩነት አለ?የሚል ነበረ ጥያቄውን ለመመለስ መረጃው በገላጭ ስታስቲክስና በነጠላ ናሙና *'ቲ- ቴስት'* ተተንተኗል፤ ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.3 ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ 4.3የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ንፅፅር በድርብ ናሙና ቲ-ቴስት

| **ትምህርት ቤት** | **ናሙና** | **አማካኝ /m/** | **መደበኛ ልያት /sd/** | **የ "ቲ" ዋጋ t-value** | **የነፃንት ደረጃ /df/** | **ጉልህነት በባለ ሁለት ጫፍ/p/** |
|---|---|---|---|---|---|---|
